**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ሚያዚያ 23/2004 ዓ.ም
(ሜይ ዴይ 2012)

**ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም.**
**አለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን**

# *አላከትም ያለ የሠራተኛው የመከራ ኑሮ*

የዘንድሮውን የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን የምናከብረው ለሠራተኛው መብት መከበርና ደህንነት ሲሉ የሕይወት ዋጋ የከፈሉትን እንደነ አበራ ገሙ፣ ማርቆስ ሀጎስ፣ ዳሮ ነጋሽና ሌሎችም በርካታ ቆራጥና ጀግና መሪዎች በማስታወስና እንዲሁም አሁንም ለሠራተኛው መብት መከበር መስዋዕትነት እየከፈሉ ያሉትን የኢትዮጵያ ሠራተኞችና በዓለም አካባቢ ያሉ አቻዎቻቸውን በማድነቅ ነው። በዚህ ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሠራተኞች ቀን ሲከበር ሰማዕቶቻቸውን ለመዘከር የመብት ጥያቄዎቻቸውን ለአሰሪዎቻቸውም ሆነ ለአገዛዙ በይፋ ሰላማዊ በሆነ መልኩ ለማቅረብ፡ የታሰሩ ሠራተኞች ከእስር እንዲፈቱ፤ ለድርጅት አልባነት የዳረጋቸው ሁኔታ ተወግዶ የተነጠቁትን ማህበራቸውን አለምንም ጣልቃ ገብነት በአዲስ መንፈስ በራሳቸው ለማደራጀት እንዲችሉ፤ ሠራተኞች የማይገረሰሰው ተፈጥሯዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው መጠየቅ ኢሕአፓን የመሰሉ የማንኛውም ሀገር ወዳድ ድርጅቶችና ግለሰብ ዜጋ ኃላፊነትና ግዴታ ነው።

በአምባገነን ወታደራዊ አገዛዝ ዘመን በአንዲት የጭንቀት ድባብ በሰፈነባት የሠራተኛ ቀን ብቻ ከ1200 በላይ የሚሆኑ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በአሰቃቂና በግፍ መጨፍጨፋቸውን ከሕሊናችን ምንጊዜም የማይጠፋ ዛሬም ድረስ በሀዘንና በቁጭት የምናስታውሰው ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ለላብ አደሩና ለሠራተኛው ያለው ልዩ ቅርበትና አመለካከት ከፍተኛ በመሆኑ ይህ ቀን ሲከበር ለትግል አጋር ያለውን ድጋፍ በመግለፅ ብቻ ሳይሆን የሚያከብረውና የሚያስታውሰው የሕይወት ግብር የከፈሉትን የጋራ ሰማዕቶቻችንን በጋራ በመዘከርም ጭምር ነው።

ያለፉትን 21 አመታት በጥሞና ለሚያሰላስል ማንኛውም ዜጋ ሁሉ የወቅቱ ሁናቴ ካለፉት ሁለት አገዛዞች ጋር ሲነፃፀር የኢትዮጵያ ሠራቶች የስቃይ ኑሮ በጎሰኛው የመለስ አምባገነን አገዛዝ ዘመን የከፋና የባሰ እንደሆነ ይገነዘባል። ከሁሉ አስቀድሞ የመለስ አገዛዝ የሠራተኞች ጠንካራ መሪዎችን ለእስርና እንግልት፣ ለአካልና የመንፈስ ስብራት ከመዳረጉ ሌላ፤ ደብዛቸውን ማጥፋቱና ሌላ በስንት መስዋዕት የገነቡትን ድርጅታቸውን በተለጣፊዎች እንዲነጠቁ ማድረጉም የሚዘነጋ አይደለም። ይህንና ሌሎችም በመሰሪ ተንኮልነት የታጀቡ ድርጊቶቹን በሠራተኛው ላይ ከፈፀመ በኋላ ሠራተኛውን በጎሳ ከፋፍሎ መብታቸውንም የሚደፈጥጥ አፋኝና ጨቋኝ ሕግ መደንገጉን በስፋት ቀጠለበት። ለኑሮ መሻሻል፡ ለመብታቸው መከበር፡ ለደሞዝ ጭማሪና የተለያዩ ሌሎች ጥቅሞችን ለማግኘት የሚታገሉበትን ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ የማድረግ መብታቸውን በመገደብ የወደፊት እድልና እጣቸውን የሀገሪቷን ለም መሬት በመቀራመትና ሀብቷን በመዝረፍ ላይ በሚገኙ የባዕዳን አሰሪዎች እጅ እንዲወድቅ በመፍቀዱ ለከፋ የባርነት ተግባር ተዳርገዋል።

በዚህ ብቻ አላቆመም። ከሩቅ ምሥራቅ ተሯሩጠው ለመጡ ቻይናዊ አሰሪዎች በነሱ እይታ "ሰነፍ": "ልግምተኛ": በሚሏቸው ሠራተኞቻቸው ላይ ሰብዓዊነት በጎደለው ደረጃ እንዳሻ የመደብደብና እርምጃ የመውሰድ መብት በመስጠቱ የሠራተኞቹ እሮሮና ጩኸት ሰሚ በማጣት ሳቢያ ለፍትሕና ለእንክብካቤ እጦት ተዳርገው ለቀጣሪዎቻቸው በግል አገልጋይነት እንዲሰማሩ ተገደዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በወንጂና በመተሃራ ፋብሪካ ሠራተኞች ላይ የደረሰው ጉዳት በሠራተኛው ሕሊና ውስጥ አሁንም ድረስ የሚታወስ ቁስሉ ያልሻረ ክስተት እንደሆነም የሚዘነጋ አይደለም።

የብር የምንዛሪ አቅም በየጊዘው ከማሽቆልቆሉ፤ የተበላሸ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ከመሆኑ፤ ቁጥጥር የለሽ ሙስና በሁሉ ደረጃ ከመስፋፋቱና ከሌሎች ማህበራዊ ቀውሶች ጋር ተያይዞ በሠራተኛው ላይ እየደረሰ ያለው የኑሮ ጉስቁልና ከምንጊዜውም በበለጠ በከፋ ደረጃ ቀጥሎ ይገኛል። ሠራተኛው በኑሮ ውድነት፤ በድህነት፤ በሥራ አጥነትና ተዛማጅ በሆኑ ችግሮች ሳቢያ እየተሰቃየ ከድህነት ወለል በታች ከሞት አፋፍ በላይ ለመኖር እየተገደደ ባለበት ወቅት ባብዛኛው ከአንድ ጎሳ የተውጣጡ የአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች ያለምንም ይሉኝታና ሃፍረተቢስነት ሠራተኛውን እየበዘበዙ መጠነ ሰፊ የሆነ ሀብት እየተቀራመቱ ይገኛሉ። የኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ደረጃ ከጊዜ ወደጊዜ ወደ ላይ እያሻቀበ በመሄዱ የተነሳም በአገዛዙ ቁንጮ ተነግሮ የነበረው በቀን ሦስት ጊዜ ምግብ የማግኘት ሁናቴ በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የማይታይና የማይዳሰስ ሆኖባቸዋል። ሴት ሠራተኞች እንደ አቻዎቻቸው የወንድ ሠራተኞች ለድካማቸው እኩል የደሞዝ ክፍያ የማግኘት መብታቸው አሁንም ድረስ አይከበርላቸውም። በርካታ ወጣት ሴት ሠራተኞች የኑሮ ሁኔታ አስከፊ በመሆኑ የተነሳም በአገዛዙ ዋና አቀናባሪነት ለዘመናዊ ባርነት ለዳር ድንበር ተሻጋሪነት ተዳርገው አሳዛኝ በሆነ መብት አልባ የስቃይ ኑሮ ለመኖር ተገደዋል። ለስለስ ባለ ደረጃ ለመግለፅ የአሁኗ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ለጭንቀት ኑሮ የተመቻቸች ነች ቢባል ሁኔታውን በግልፅ የሚናገር ይሆናል። ዛሬ ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን ሲከበር በሚገባ መተላለፍ ያለበት ቁም ነገር ይህ ሁናቴ በዚህ መልክ በምንም አይነት እንዲቀጥል መደረግ እንደሌለበትና እንዲወገደም አስፈላጊውን ጥረትና ትግል ማድረግ እንደሚገባ ነው።

የዘንድሮው ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን በኢትዮጵያ የሚከበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጠቃላይ በመለስ አገዛዝ ላይ እያደረገ ያለው ተቃውሞ እንቅስቃሴ ሂደት በቅርቡ የእስልምና እምነት ተከታይ ዜጎቻችንና መምህራን ወገኖቻችን በበኩላቸው የጀመሩት ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እየጨመረና እየጎለበተ ባለበት ወቅት በመሆኑ የዘንድሮው የሠራተኛው ቀን ክብረ በዓል ልዩ ትኩረት እንደሚያገኝ ምንም ጥርጥር የለንም። የኢትዮጵያ ሠራተኞችና ላብ አደሮችም በተመሳሳይ መልኩ ይህንኑ ፈለግ ከተከተሉና እንቅስቃሴውን ከተቀላቀሉ በተባበረ ትግል የአገዛዙን እድሜ በማሳጠር የሕዝባችን የረዥም ጊዜ የዴሞክራሲ፡ የመብት መከበር፡ የመልካም አስተዳደርና የሕግ የበላይነት እጦት ላንዴም ለሁሌም ማክሰም እንደሚችሉ ምንም ጥርጥር የለንም።

በመሆኑም ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ራሳቸውን እንዲያደራጁና መብታቸውን ለማስከበርና ሀገሪቷ ከምንጊዜውም በላይ ለምትፈልገው የትግል እንቅስቃሴ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የትግል ጥሪውን ያስተላልፋል። ኢሕአፓም በበኩሉ በዚህ ተልዕኮ ከላብ አደሩና ከሠራተኛው፣ ከእስልምና ክርስትና እምነት ተከታዮች፣ ከመምህራኑ ማለትም ከኢትዮጵያ ጭቁኑ ሕዝብ ጎን በመሆኑ ድርሻውን ለመወጣት ካሁን በፊት የገባውን ቃል በዛሬው እለትም በአዲስ መንፈስ እያደሰ የሚታገል መሆኑን ይገልፃል። ኢሕአፓ ምንጊዜም በትግሉ ሜዳ እንደሚገኝ በቅርቡ በአዲስ አበባ ያደረጋቸው የይፋ የቅስቀሳ ተግባር ይመሰክራሉና ከጎናችሁ ለመሆኑ ማረጋጋጫ ነውና በጋራ እንታገል ሲል የአደራ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ድል ለላብ አደሩና ለሠራተኛው!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን ይለምልም!!

እናቸንፋለን!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France